ሀይማኖታዊ ሽፋን

ከ:-ምንተስኖት አለማየሁ

2012 ዓ'ም

የመጀመሪያ:-መፅሀፍ

ይህ ሀይማኖታዊ ሽፋን:- በሚል ርዕስ የተዘጋጀው ፅሁፍ የስህተት አስተምሮን ፍጹምነትን በተላበሰው በመጽሀፍ ቅዱስ እየመረመረ ክህደትን በግልጽ ነቅሶ ያወጣል። አንባቢውንም ቅዱስ ቃሉ ላይ ብቻ ተንተርሶ ህይወት የሚገኝበት ትምህርት የትኛው እንደሆነ ከቃለ እግዚአብሄር እያሳየው ሀዋርያት በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው በጻፉት ወንጌል ላይ ብቻ እንዲታመን ይረዳዋል።

➽እግዚአብሄር አምላክ መጽሀፍ ቅዱስን ለሰዎች የሰጠበት ምክንያት ራሱን/እግዚአብሄርን/ ብቻ እንድናመልከውና እንድናከብረው ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሶስት አመት ተኩል ተመላልሶ ባስተማረበት ወቅት አስተምህሮቱ እውነተኛ አስተማሪውም/ኢየሱስ/

ጳድቅ ነበር። ይሁን እንጂ ጌታችን ካረገና ሐዋርያቱም ለታመኑበት አምላክ ሰማዕት ከሆኑ በኋላ የክህደት አስተምህሮን ከሀዲዎች ወደ ቤተክርስቲያን ማስገባታቸውን አላቋረጡም። ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል አርዮስ- ክርስቶስ የእግዚአብሄር መለኮታዊ ልጅ አይደለም ብሎ በተነሳ ጊዜ ትምህርቱ አዲስ ኪዳንን ፈጽሞ መሠረት ያደረገ አልነበረምና በጊዜው ከስሟል። ቢከስምም ሶስት መቶ አመታትን ቆጥሮ ለእስልምና መሠረቱን ሳይጥል አልቀረም። ወደ ዋናው መነሻዬ ልመለስና ክርስቲያኖች ተብለው በሚጠሩ ሀይማኖቶች መካከል ልዩነትን ስለፈጠረው ምክንያት ቆም ብለን ብንጠይቅ! ምን ይሆን እንዲህ እዚህና እዚያ ጥግ ሁነው ትችትንና ሌሎች ኢ-ክርስቲያናዊ ንግግሮች ላመኑበት ነገር እንዲስተዋሉበት የፈቀደው ብንል። ምንጭ የሚሆነው አንድአንዶች ቃሉን እንዳሻቸው እየተረጎሙ ሌሎችን እየነቀፉ የሚሰብኩት ስብከት እንዲያውም ከሚያስተምሩት ትምህርት ጋር በቀጥታ ስለሚጋጭባቸው ቃላቱን ቀይረው እስከማሳተም ድረስ ልባቸውን አደንድነዋል። እነርሱ ከቃሉ ውጭ በሀይማኖት ስም ሽፋን ሰጥተውት የልባቸውን ምኞት ቢያስተምሩም እግዚአብሄር አምላክ እውነተኛ ተከታዮቹን ግን ፈጽሞ አያጣም። በጣም የሚያስገርመው ነገር ደግሞ ተከታዮቻቸው/ ምዕመኑ/ የመጽሀፍ ቅዱስ ቃላትን የመጀመሪያውን ደልዘው የራሳቸው መሻት የሆነውን በተደለዘው ቦታ

ቢያስገቡትም ሀሳባቸው አልሞላ ሲል ሌላ ድርሰቴ ሲያዘጋጁ ለምን እንኳ ብለው አይጠይቁም። አስተማሪዎቻቸውም ጠያቂ በመጥፋቱ የእግዚአብሄር ቃል ላይ እንዲፋንኑ መንገድ የተጠረገላቸው ይመስላል።

❣ አሁን ደግሞ በክርስቲያኖች መካከል ልዩነት ለሆኑት ዋና ዋና ምክንያት እንመልከት:-

❶ ምልጃን በተመለከተ

❷ ግለሰብን በተመለከተ የሚሉት ናቸው።

ስለምልጃ እንዲሁ በአንድ ጊዜ የተጻፈውን ነገር ከመደምደም በፊት ለአዲሱ ኪዳን ብሉይ ኪዳን ጥላ ነውና ከመጀመሪያው ተነስተን ወደ ፍጻሜው እንሂድ። በብሉይ ኪዳን ኦሪት ዘሌዋውያን ም፬:፫፪-፫፭ እና ም፭ ላይ አንድ ሰው ስለ ሠራው ሀጢያት መስዋዕት ጠቦት በግ ወይም ፍየል ገንዘቡ የማይበቃ እንደሆን ሁለት ዋኖስ ይዞ ይሄዳል ካህኑም ሀጢያቱን ያስተሰረይለታል። ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ ማን ነው! የሰዎችን ሀጢያት ሊያስተሰረይ የሚችለው ብለን ብንጠይቅ ከጌታችንና ከመድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ውጭ ፈጽሞ ሊገኝ አይችልም። በ፩ኛ ዮሐንስ መልእክት ም፪ ቁ፪ ላይ እርሱም የሀጢያታችን ማስተሰሪያ ነው።ለሀጢያታችንም ብቻ አይደለም ነገር ግን ለዓለሙ ሁሉ ሀጢኃት እንጂ። እናም በብሉይ እና በአዲስ ኪዳን ልዩነቱ እጅግ ሰፊና ድርጊቱ የሚከወነው እንደሙሴ

ህግ ከላይ እንዳነበባችሁት ሲሆን በአዲስ ኪዳን ግን የእንስሳት ደም ሳያስፈልገን አንድ ጊዜ በፈሰሰው ከበግና ከዋኖስ የሚበልጥ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም ነው። ለዚህም ድጋፍ እንዲሆነን በዕብ ምዕ ከተናገርነውም ዋናው ነገር ይህ ነው በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህን አለ። ሚለውን ቃል ማስረጃችን ይሆነናል። ይህ የክርስቶስ ክህነት በእንዲህ እንዳለ ማርያም በምን እሳቤ የሰውን ሀጢያት ልታስተሰርይ ትችላለች ብለን ብንጠይቅ መልሱ በምንም ልታስተሰርይ እንደማትችል እሙን ነው። እንደውም ኢየሱስን ወልዳ ሉቃ፪-፪፬ እንደሙሴ ህግ ዋኖስ ይዛ መስዋዕት ለማቅረብ ወደ ኢየሩሳሌም ወስዳዋለች። ሴት ወንድ ልጅን ከወለደች በኋላ የሚደረገውን የመንጻት ስርዓት በኦሪት ዘሌዋውያን ም፭፪ ላይ ማንበብ በቂ ነው። ራሱን ስለ እኛ ሀጢያት መስዋዕት ያደረገው መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ይማልዳል ሲባል የማይዋጥላቸው ሰዎች አሉ ይሁን እንጂ መጽሀፍ ቅዱሳችን በግልጽ ሮሜ፰-፫፬ የሞተው ይልቁንም ከሙታን የተነሳው በእግዚአብሄር ቀኝ ያለው ደግሞ ስለ እኛ የሚማልደው ክርስቶስ ነው። ታዲያስ ይህን የመሰለ ግልጽ ቃል ተጽፎ እያለ ማርያም ታማልዳለች ማለት ኑፋቄ አይሆንብም! ይሆንብናል። እንደውም ሉቃ ፪፪-፫፪ ላይ ኢየሱስ ሰይጣን እንደስንዴ ሊያበጥራቸው ሲለምን እምነታቸው እንዳይጠፋ አማለድሁ ብሎ ለ ስምዖን ነግሮታል። በዕብራውያን

መልዕክት ምኟ ላይ ስለ እነርሱም ሊያማልድ ዘወትር በህይወት ይኖራልና ስለዚህ ደግሞ በእርሱ ወደ እግዚአብሔር የሚመጡትን ፈጽሞ ሊያድናቸው ይችላል። መስቀል ላይ ሆኖ እንኳ አባት ሆይ የሚያደርጉትን አያውቁምና ይቅር በላቸው ብሏል። ታዲያ እንዴት ማርያም ታማልዳለች ተብሎ ሲጠየቅ መረጃ አለን ብለው የሚያሳዩት በቃና ዘገሊላ ምኟ ላይ ያለውን ታሪክ እንደምታማልድ ያሳያል ቢሉም ክፍሉ ግን የሚናገረው ኢየሱስ የመጀሪያ ምልክቱንና ክብሩን የገለጠበት ደቀመዛሙርቶቹም በእርሱ እንዳመኑ እዚያው ቁጥር፩፩ ላይ ይነግረናል እንጂ በማርያም ምልጃ አመኑ ተብሎ አልተጻፈም። የታነጽነው በሐዋርያት መሠረት ላይ ነውና አንዲት ጥያቄ እንጠይቅ? ከ አሥራ ሁለቱ ሐዋርያት የትኛው ሐዋርያ ነው በማርያም ስም የጸለየው? ብንል ማናቸውም በማርያም ስም አልጸለዩም ይልቁንስ በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ክርስቶስ ጠበቃ፣ ዋስ፣ አማላጅ እንደሆነ ፅፈዋል። ፩ኛ ዮሐንስ መልዕክት ምኟ ላይ ልጆቼ ሆይ ሀጢኃትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ።ማንም ሐጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ዕብ ፲-፪፪ እንዲሁ ኢየሱስ ለሚሻል ኪዳን ዋስ ሆኗል። እኚን የመሠሉ ምስክሮች እንደ ደመና በዙሪያችን እያሉልን ማርያም ታማልዳለች ማለት ትልቅ ስህተት ውስጥ መግባትና የክርስቶስን የመስቀል ላይ ስራ ማጣጣልና

መናቅም ጭምር ነው። አንድ ወሳኝ ሀሳብ ልጠቁማችሁ አምላክን አምላክ ካሰኘው ነገር አንዱ በአንድ ጊዜ ያለ አንዲት ማይክሮሰኮንድ ልዩነት ሁሉም ቦታ መገኘቱ ነው ማርያም ደግሞ ፍጡር ነች በአንድ ጊዜ ሁሉም ቦታ ልትገኝ አትችልም ታዲያ በአለም ዙሪያ ያሉ በማርያም ስም የሚጸልዩ በቁጥር እጅግ ብዙ የሆኑ ክርስቲያን ነን ብለው ራሳቸውን የሚጠሩት ነገር ግን መፅሀፍ ቅዱስ የሚለውን የካዱትን ጸሎት ልትሰማ አትችልም ምክንያቱም ሁሉም ቦታ አትገኝምና። በሚሊየኖች የሚቆጠሩ አድራሻቸው ወደ ማርያም የሆኑ ጸሎቶች በዮሐ ወንጌል ም፩፬ ፩፫-፩፬ እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና አብም ስለ ወልድ እንዲከበር በስሜ የምትለምኑትን ሁሉ አደርገዋለሁ።ማናቸውንም ነገር በስሜ ብትለምኑ እኔ አደርገዋለሁ-ከሚለው ቃል ጋር ፈጽሞ የተጣረሱና ሀሰት ናቸው። እናም እስከ ዛሬ ድረስ ባለማወቅና ወይንም አውቃችሁ መፅሀፍ ቅዱስ ከሚለው ውጭ በማርያም ስም የጸለያችሁ ህይወት ወደ ሚሰጠው ወደ እግዚአብሄር ቃል ተመለሡ በኢየሱስ ክርስቶስም ብቻ የልባቹን መሻት አስታውቁ።

❷ኛው ሀሳብ ግለሰቦች በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ምን አይነት ስፍራ ነበራቸው የሚለውን የሚመለከት ሲሆን መጽሀፍ ቅዱስን አስተውለን ስናነበው እግዚአብሄር አምላክ በብሉይና በአዲስ ኪዳን የተጠቀመባቸው ሰዎች በልጅነታቸው ምን አይነት ሰዎች ነበሩ ብለን ብንጠይቅ

መጽሀፍ ቅዱስ አይነግረንም ምክንያቱም የእግዚአብሄር አላማ ለሰው ልጆች ያለውን ፍቅር ራሱን በቃሉ ውስጥ ማሳየት ስለሆነ እንጂ የሰውን ታሪክ ለመዘገብ አይደለም። ለምሳሌ ያህል ነብዩ ኢሳያስን ብንወስድ የአሞጽ ልጅ እንደሆነ እንጂ የልጅነቱን ታሪክ አልተናገረም። ነገር ግን ዛሬ ዛሬ ግን በዘመናችን ማርያምን በማምለክ አራተኛ የስላሴ አካል እስክትመስል ድረስ የእጅ ስራ የሆነ ስእል ሊኦናርዶ ዳቪንቼ የሳለውን እስከ መስገድ ድረስ ደርሰዋል እየሰገዱም ነው። ነገር ግን ለእጅ ስራ እንዳንሰግድ እግዚአብሄር ያዛል ። "አምላክህም እግዚአብሄር የከለከለውን በማናቸውም ቅርጽ የተቀረጸውን ምስል እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ አምላክህ እግዚአብሄር የሚባላ እሳት ቀናተኛም አምላክ ነውና ዘዳ ፬፣፪፫-፪፬። የተከለከለው ምስሎችን መሳልና በፊታቸውም ወድቆ መስገድ እንደሆነ ልብ ሊባል ይገባል።

Mintesinot Alemayehu our Telegram channel:-Truth